Dedicated to Excellence
Cherry Creek Schools

# በሥራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት – አፕርንትሽፕ (ስልጠና)

አፕረንትሽፕ ወይንም የሥራ ላይ ልምምዶች ተማሪው በሚፈልገው የሙያ መስክ ጥልቅ አሰሳ የሚጀምርበት እና ሰርተፊኬቶችን እና/ወይም ዲግሪውን በዚያ መስክ የሚሰራባቸው የብዙ አመት የስራ እድሎች ናቸው። ይህ አይነቱ የሥራ ላይ ልምምዶች ተማሪዎች የሚከፈላቸው የሥራ መደቦች ስሆን ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች 11ኛ ወይንም 12ተኛ ክፍል ስሆኑ የሚጀምር እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከተመረቁ ቦሃላ ከ 1 እስከ 2 ዓመታት የሚቀጥሉ ናቸው ።ተለማማጆች ቦሃላ ላይ የኩባንያው ተቀጣሪዎች ይሆናሉ እና አሁንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሆነው እያሉ ተዛማጅ ኮርሶችን ይወስዳሉ።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

- በተለማማጅነት የተቀጠሩ ተማሪዎች በመደበኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ የሚያስፈልጉትን ኮርሶች ብቻ ይወስዳሉ። የሙያ እና ቴክኒካል ትምህርት (CTE) የስልጠና ኮርስ የተመረጡ እንደ አማራጪ የሚወሰዱትን ኮርሶችን ይተካዋል እና ተማሪዎች በትምህርት ቀን ሥራ እንዲሰሩ ያስችላቸዋል።
- ተለማማጆች አግባብነት ያላቸውን ብቃቶች ለመቆጠጠር ወይም ለ ሰርትፍኬት የሚያስፈልጉትን ሰዓቶች ለመድረስ ይሰራሉ።??/
- ተማሪዎች ከሚፈልጉት የሙያ መስመር ጋር የሚዛመድ ትምህርት ይቀበላሉ በ (ኮንከረንት/ዷኅል እንሮለመንት፣ የትምህርት ክፍያ ወይም የምስክር ወረቀት ለማግኘት ድጋፍ)??
- ተማሪው በትምህርት ቀን በከፊል እንዲሰራ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርሶችን እንዲወስድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብሮች በዝህ መልክ ተዘጋጅተዋል።

ለቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ተማሪዎች የተለያዩ የሥራ ላይ የልምምድ እድሎች አሉ። የኩባንያውን እና የተማሪን ፍላጎቶች ለማሟላት እያንዳንዱ እድል ልዩ የሆነ የማመልከቻ ሂደት እና ልዩ መስፈርቶች አሉት. ። ተማሪው የስራ ልምድን በሚሰጥ አሰሪው በተገለፀው መሰረት የቅጥር እና ብቁነት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

## እንዴት ማመልከት እንደሚቻል፡-

1. የCCSD የስራ ቦርድ ለቀጣዩ አመት ያሉትን የሥራ ላይ ልምምዶች ክፍት ቦታዎችን በስፕሪንግ ሴሚስተር ይከፈታል።
2. ተማሪዎች አጠቃላይ ማመልከቻ ይሞላሉ እና አንዳንድ ተማሪዎች ከአሰልጣኝ ቡድን እና ከኩባንያው ጋር ቃለ መጠይቅ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ. እያንዳንዱ የሥራ ላይ ልምምድ ዕድሎች የተለያዩ መስፈርቶች እና ሂደቶች አሉት።

ተማሪዎች ከተመረጡ እና የሥራ ላይ ልምምድ የስራ መደቦችን ከተቀበሉ፣ በልምምድ ሴሚናር ውስጥ ይመዘገባሉ. እንዲሁም የቅጥር እና የቅጥር ሂደቱን ከቀጣሪው ጋር ይጀምራሉ።

- **አብዛኛዎቹ የስልጠና ስራዎች ከዲስትሪክቱ የCTE የሙያ እና የቴክንክ መስመሮች ጋር የተጣጣሙ ናቸው። የሙያ መንገዶቹ ምንድርናቸው?**
- የንግድ አስተዳደር
- የሚዲያ ጥበባት
- እንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ
- ምህንድስና እና ቴክኖሎጂ
- የጤና ሳይንስ
- ህግ፣ የህዝብ ደህንነት፣ እርማቶች እና ደህንነት
- መስተንግዶ እና ቱሪዝም

- ሰብአዊ አገልግሎቶች
- አርክቴክቸር እና ግንባታ
- ማኑፋክቼሪንግ
- መጓጓዣ, ስርጭት እና ሎጂስቲክስ
- የውጪ መዝናኛ አመራር

*የሥራ ላይ ልምምዶች በእያንዳንዱ በላይ በተጠቀሱት መስመሮች ላይ  ላይገኙ ይችላሉ። ልምምዶች ከአመት ወደ አመት ይቀየራሉ.*

በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁሉም ከላይ የተጠቀሱት ኮርሶች  አይሰጡም። Contact your school counselor or refer to the school's course guide for more information. ለበለጠ መረጃ የትምህርት ቤቱን የትምህርት አማካሪን ያነጋግሩ ወይም የትምህርት ቤቱን የኮርስ መመሪያ ይመልከቱ።

**ለበለጠ መረጃ**

የተማሪውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ ያነጋግሩ
በስራ ላይ የተመሰረተ የመማሪያ ቡድንን ያነጋግሩ
(Tara Bell,)የድህረ ሁለተኛ ደረጃ የስራ ኃይል አስተዳዳሪ, tbell18@cherrycreekschools.org
(Ashlin Montgomery)የስልጠናዎች አጋር amontgomery12@cherrycreekschools.org
Margaret Krob, (ረዳት), mkrob@cherrycreekschools.org